## የፍልስፍናው ዶክተር ተሰማ ብስራት ኅልፈት

**አሲምባ ታሪካዊው የተጋድሎ ቦታ ያለባት የትግራይዋ ኢሮብ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ምሁራን ያፈራች ናት፡፡ ከነዚያም መካከል አንዱ ባለፈው ሰኞ ሥርዓተ ቀብራቸው በአዲስ አበባ የተፈጸመው ዶክተር ተሰማ (ተክለሃይማኖት) ብስራት ናቸው፡፡**

በካፑቺን ፍራንቸስካና የፍልስፍና እና የነገረ መለኮት ተቋም፣ የፍልስፍና መምህር የነበሩት ዶክተር ተሰማ፣ ከ1975 ዓ.ም. ጀምሮ በቀድሞው መንግሥት የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ ግንኙነት መምሪያ በምርምር ዘርፍ ውስጥ በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ለ13 ዓመታት አገልግለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም አቀፍ ጉባኤ ከ22 ዓመት በፊት ተሳታፊ የነበሩት ምሁሩ፣ በዲፕሎማትነት ልዑካንን ባሕር ማዶ መርተው መሔዳቸው፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) የመሪዎች የተለያዩ ጉባኤዎች ላይ ተሳታፊ እንደነበሩ ገጸ ታሪካቸው (ሲቪ) ያመለክታል፡፡

በትግራይ ምሥራቃዊ ዞን ኢሮብ ወረዳ አሊተና ከተማ ጥር 25 ቀን 1935 ዓ.ም. ከአባታቸው አቶ ብስራት ገብራይና ከእናታቸው ወይዘሮ አምለሷ የተወለዱት ዶክተር ተሰማ፣ የመጀመርያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲግራት ከተማ ጽንሰታ ለማርያም ትምህርት ቤት አጠናቀዋል፡፡

ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ጣሊያን በመሔድም በተለያየ ዘመን (ከ1961-1973 ዓ.ም.) ከዑርባኒያ ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና የመጀመርያ ዲግሪ፣ በነገረ መለኮት (ቲኦሎጂ) ዲግሪ፣ እንዲሁም ከሮም ስቴት ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካ ሳይንስ የዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል፡፡ የኢንተሌጀንሲ ጥናትም በቼኮዝሎቫኪያ (1978 ዓ.ም.) ተከታትለዋል፡፡

ሳሆ (የኢሮብ ቋንቋ)፣ ትግርኛ፣ ግእዝ፣ አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽና ላቲን ያውቁ የነበሩት ሊቀ ልሳናት ዶክተር ተሰማ፣ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ሕክምና ሲከታተሉ ቆይተው ያረፉት መጋቢት 22 ቀን 2005 ዓ.ም. ነበር፡፡ በማግስቱም በጴጥሮስ ወጳውሎስ የካቶሊክ መካነ መቃብር ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡

በአሲምባው የኢሕአፓ የትግል ዘመን ፊታውራሪ ከነበሩት ከኢሮብ ተወላጆች ከነዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የትግል አጋርነት እንደነበራቸው የሚነገርላቸው ዶክተር ተሰማ ብስራት ባለትዳርና የሦስት ልጆች አባት ነበሩ፡፡